
Secrets of

**የመጀመሪያ ዕትም**

# ስኬታማ ጥናት



በአጭር ጊዜያት፣ ብዙ ሳይደክም ከፍተኛ ግሬድ
ለማግኘት የሚያስችሉ ሳይንሳዊ የአጠናን፣
የአተዋወስና የፈተና አሰራር ጥበቦች

በዶ/ር አቡሽ አያሌው

ሌይአውትና ዲዛይነር
ሒሩት ይትባረክ

## መታሰቢያነቱ

ይህ መፅሐፍ ለምወዳቸው ልጆቼ ለፋኑኤል አቡሽና ለአዶናይ አቡሽ እንዲሁም ከጎኔ ሆና በፅኑ ላበረታታችኝ ባለቤቴ ወ/ሮ ፀሐይ ሳህሌ ይሁንልኝ።

© COPY RIGHTS RESERVED
የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

**1998 ዓ.ም አዲስ አበባ**

በመፅሐፉ ዙሪያ የታዘቡትን ማናቸውንም አስተያየትዎን በስልክ ወይንም በደብዳቤ ይግለፁልን
ስልክ፡- 0911- 40 47 92
አደራሹ፡- ማዕከል አሳታሚ ድርጅት (መፅሐፍ ዝግጅት ክፍል)
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
ፖ.ሳ.ቁ፡- 26622/1000



# የጥናት ፕሮግራምና የጊዜ አጠቃቀም

# የተሳካ የተነሳሽነትን መንፈስ ለተሳካ ጥናት ለማዋል

"በምድር ላይ እጅግ ውድ የሆነውን ንብረት ተቀብሮ የምናገኘው የት ነው? የአልማዝ ወይም የወርቅ ማዕድናት የሚገኙበት ስፍራ? አይደለም፤ ከፍተኛ የነዳጅ ድፍድፍ ያለበት ምድር? በፍፁም! እጅግ ውድ የሆነውን ንብረት የምናገኘው በመቃብር ስፍራዎች ነው፡፡ ማድረግ የሚችሉትን ሳያደርጉና ያላቸውን እምቅ ኃይል (potential) ሳያወጡ ያሸለቡ ሰዎች ናቸው ውዱን ንብረት እንደያዙ እንደተቀበሩ የሚቆጠሩት" ሬቨረንድ ማይልስ ሙንሮ

ብንጠቀምበት በራሳችንም ሆነ በሌሎች ህይወት ላይ ታላቅ ለውጥ ልናመጣበት የምንችለውን እምቅ ኃይላችንን አስመልክቶ የተነገረ ግሩም አባባል ነው ከላይ ሰፍሮ የምናገኘው፡፡ ሆኖም በተለይ የትምህርት ህይወትን በተመለከተ ስኬት እንዳናገኝ እንቅፋት የሚሆንብን ያለንን ሃይል በቅጡ አለማገናዘብና ራስን አሳንሶ ማሰብ በማምጣር ቀዳሚነት ይመጣል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ጥናትና በቀላሉ ልማዶች የስኬታችን እንክን እንዳይሆኑ ለማየት ሞክረናል፡፡

"ልማድ" (habit) አሊያም "ባህሪይ" ብለን የምንጠራው ሁሉ [illegible] ያስለመድነውን ነገር ከምናስበው ስሩ ያለ እንደሆነ አይተናል፡፡ በህይወታችን ያለን [illegible] ያለን ቁርጠኝነት፣ ማህበራዊ ህይወታችን፣ ኢኮኖሚያዊና ግላዊ [illegible] በሙሉ በዚህ ሃሳብ ስር እንደሚጠቃለሉ አይተናል፡፡

[illegible] ጥናት እንክን ሊሆኑብን የሚችሉትን እንቅፋቶች በዚህ መልክ [illegible] እንችላለን (ዝርዝሩን ከታች ይመልከቱ) ችግሮቻችንን በቀጥ [illegible] ወደ መፍትሄዎቹ መጓዝ የምንችለው፡፡ "ስለሆነም" የትኞቹ [illegible] ብለን ራሳችንን እንጠይቅ፡፡

በኮሌጅ ተማሪዎች ደረጃ የተሰራ የጊዜ ፕሮግራም ናሙና

| | Mon. | Tues. | Wed. | Thurs. | Fri | Sat. | Sun. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7-8 | ← | Dress | And Break | Fast → | → | → | |
| 8-9 | History | | History | | History | Dress + Breakfast | |
| 9-10 | | Phy. Ed | | Phy. Ed. | | Phy. Ed. | Dress+ Breakfast |
| 10-11 | | Chem. | | Chem. | | Chem. | |
| 11-12 | French | | French | | French | | |
| 12-1 | ← | | Lunch | → | | | → |
| 1-2 | Math | Filmmaking | Math | Filmmaking | Math | | |
| 2-3 | | | | ↑ | | | |
| 3-4 | | | | Chem. lab. | | | |
| 4-5 | English | | English | ↓ | English | | |
| 5-6 | | | | | | | |
| 6-7 | ← | | Dinner | → | | | → |
| 7-8 | | | | | | | |
| 8-9 | | | | | | | |
| 9-10 | | | | | | | |
| 10-11 | | | | | | | |
| 11-12 | ← | | Sleep | → | → | | |

***ናሙና 1.*** ይህ ከሰኞ-እርብ ያለውን የትምህርት ክ/ጊዜና አይነት የሚያሳይ ሰሌዳ ነው። ከዚህ ውጭ ያለው ጊዜ ትርፍ የማጥኛ ጊዜ ይሆናል ማለት ነው። በየትኛው ትርፍ ጊዜ የትኛውን የትምህርት አይነት ማጥናት እንደሚገባ በሚቀጥለው ቻርት ላይ ተመልከቱ።

# እየሠሩ ለሚማሩ ተማሪዎች የጊዜ አጠቃቀም ስልት

ሥራ እየሠሩ በትርፍ ሰዓት የሚማሩ ተማሪዎች መቼም የተትረፈረፈ ጊዜ ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በተለይም በሥራቸው ምክንያት ድካም ሊኖርባቸው ስለሚችልና በቂ ጊዜም ስለማይኖራቸው የራሳቸውን ሁነኛ የጥናት መንገድ መጠቀም አለባቸው፡፡ እስኪ እጅግ ጠቃሚ የሚባሉትንና በሥራ ላይ ሆነው ለሚማሩ ተማሪዎች ተመራጭ የሆኑትን የጊዜ ቁጠባና የጥናት ስልት እንመልከት፡፡

- አጫጭር ኖቶችን በማዘጋጀት መስተዋትና ግድግዳ ላይ እንዲሁም ሲወጡ ሲገቡ በቀላሉ ሊያዩዋቸው በሚችሉባቸው ሥፍራዎች በመለጠፍ ፀጉርን ሲያበጥሩም ሆነ ሌላ ተመሳሳይ ሥራ በሚሠሩበት ወቅት በዚሁ አጋጣሚ እነኚህን ወረቀቶች የመቃኘት እድል ይኖራቸዋል፡፡
- አነስ አነስ ያሉ ካርዶችን በማዘጋጀት ከእነሱም ላይ ጠቃሚና ሊነበቡ የሚገባቸውን ፅሁፎች በማስፈር በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የማንበብ ዕድል እንዲኖር ማድረግ፤ እነኚህን ወረቀቶች ከኪስና ከቦርሳ አለመለየት ለአፍታም ቢሆን ሥራ ሲፈቱ እየት እየት ማድረግ ይችላሉ፡፡

በትምህርት ክፍለ ጊዜ ወቅት የተማሩትን በካሴት በመቅዳት መኪና ውስጥ ሆነው ወይም በሌላ ሥፍራ (እቤት) ሌላ ሥራም እየሠሩ ማዳመጥ መቻል ይኖርባቸዋል፡፡

# ለሁሉም ጊዜ አለው፤ ለማጥናትም፣ ለመዝናናትም፣ ለመዘናጋትም!

ስለጥናት ሲታሰብ የመጀመሪያውና ትልቁ እንቅፋት የሚሆነው ተማሪው በሙሉ ተመስጦ የሚያጠናበት መደበኛ ጊዜ መኖር አለመኖሩ ነው፡፡ የተማሪዎች ሥነ ልቦና ጥናት እንደሚያሳየው የተወሰነ የጥናት ፕሮግራም



# የስኬታማ ጥናት ምስጢሮች

## ጊዜ ቆጣቢ፣ ጉልበት ቀናሽ፣ ውጤት አንበሽብሽ

- "There are three reasons why...." (HERE THEY COME!)
- "First...Second... Third...." (THERE THEY ARE!)
- "And most important,...." (A MAIN IDEA!)
- "A major development...." (A MAIN IDEA AGAIN!)
- He may signal support material with:
- "On the other hand...."
- "On the contrary...."
- "For example...."
- "Similarly...."
- "In contrast...."
- "Also...."
- "Further...."
- "Furthermore...."
- "As an example...."
- "For instance...."

He may signal conclusion or summary with:

- "Therefore...."
- "In conclusion...."
- "As a result...."
- "Finally...."
- "In summary...."
- "From this we see...."

He may signal very loud with:

"Now this is important...."

- "Remember that...."
- "The important idea is that...."
- "The basic concept here is...."

Signals are usually ignored by those of us who do not know how to listen effectively. Expect signals and be alert when you receive them.




አሁን ወደ ዋናው የኖት አያያዝ ሂደት እናምራ:: ይህን ስልትም ስንጠቀም የግራውን ክፍት ቦታ፣ የቀኙን ሰፊ ቦታና የታችኛውን ሦስተኛ ክፍት ቦታ ልብ እያልን እንቀጥል።

## 1 Record (ሁሉንም ፃፍ):-

በቅድሚያ ኖት ከመያዝህ በፊት የቶፒኩን ስም፣ የአስተማሪውን ስምና ቀኑን ከገፁ አናት ላይ ፃፍ:: ከዚያም በክፍል ውስጥ ያገኘኸውንና የቻልከውን ነገር ሁሉ ለመፃፍ ሞክር:: አውቀዋለሁ ወይም አንብቤዋለሁ በሚባል ከንቱ የማታለያ ሃሳብ አትታለል:: የትኛውም መረጃ እጅግ ጠቃሚህ ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ኖት ከሳምንት በኋላ ሲነበብ ታዳያ

**Common Standard Symbols:**

| | | | |
|---|---|---|---|
| + | and | w/ | with |
| vs | versus | ∴ | therefore |
| S | subject | Ss | subjects |
| n° | degrees | n' | minutes |

**Common Standard Technical Symbols:**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ∠ | angle | ‖ | parallel |
| ≡ | identical to | → | leads to, approaches |
| ln | natural logarithm | ↕ | vibration, motion |
| m | mass | □ | area |
| ∫ | integral | ∝ | varies directly as |
| $\overline{\vert\vert\vert}$ | base, foundation | ∼ | sine curve, cosine curve |
| < | less than | > | greater than |
| ≥ | greater than or equal to | f | frequency |

**የቃላቶችን የመጀመሪያ ፊደል ነጥሎ በመሰብሰብ (ለምሳሌ):-**

| | |
|---|---|
| NYC | NewYorkCity |
| GOP | Grand Old Party |

**የቃሉን የመጀመሪያ ተነባቢ ክፍል ተጠቀም (ለምሳሌ):-**

| | |
|---|---|
| intro | introduction |
| bio | biology |
| max | maximum |
| rep | repitition |
| Min | minimum |

**የቃላቱን የመጀመሪያና ሁለተኛ ተነባቢ ፊደላትን በመጠቀ… (ለምሳሌ):-**

| | |
|---|---|
| subj | subject |
| cons | consquences |
| ind | individual |
| rep | repitition |

**ከቃላቶች መሃል ያሉትን አናባቢ ፊደላት በማውጣት (ለምሳሌ):-**

| | |
|---|---|
| bkgd | background |
| sysm | system |
| ampltd | amplitude |
| estmt | e[illegible]mate |
| frdm | freedom |
| 1st | first |
| 2nd | second |
| 3rd | third etc. |

**የአፖስትሮፍ ጭረቶችን በመጠቀም (ለምሳሌ):-**

| | |
|---|---|
| am't | amount |
| gov't | government |
| cont'd | continued |

ብዙ ነገሮችን የሚገልጡ ቃላት (Plurals) ላይ «S» መጨመር (ለምሳሌ):-

| | |
|---|---|
| Fs | forces |
| chaps | chapters |
| /s | ratios |
| 1920s | i.e. 1920-1929; similarly 1970s etc. |

በ «ing» የሚያልቁ ቃላት ላይ የአፖስትሮፍ ጭረትና «g» ፊደልን በመጠቀም (ለምሳሌ):-

| | |
|---|---|
| chk'g | checking |
| tch'g | teaching |
| lrn'g | learning |

የቋንቋ ጠቋሚዎችን (articles) ማስወገድ (ለምሳሌ):-

a
the

አላስፈላጊ ግሶችን መተው (ለምሳሌ):-

went came be

አጫጭር ቃላትን በምህፃረ ቃል ለማሳጠር አለመሞከር (ለምሳሌ):-

in so but
to
if

አዶኑቶች በተለይ ተጨማሪ ጥያቄዎችንና ፕሮብሌሞችን ከማመሳከሪያ መፅሃፍ ወስዶ መስራት በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

*ጥናት በትብብር ወይስ በጫበጣ?*

# የግሩፕና የግል ጥናት ያላቸው ጥቅምና ጉዳት

*"ብቻውን የሚሮጥ የሚቀድመው የለም" ሃበሻዊ ብሂል*

"United we stand divided we fall" *("በንተባበር እንቆማለን፣ ብንነጣጠል እንወድቃለን" እንደማለት) የማዶ አገር አባባል*

በእርግጥም ብቻውን በሚሮጠው ሯጭ አይን ሲታይ እንድም የሚቀድመው ሰው አይኖርም። ምን ያክል እንደ ፈጠነና እንደዘገየ፣ ምን ያክል ብርታትና ድካም እንዳለው የሚለካበት መስፈርት የለውማ! ከሌሎች ጋር የሚወዳደርበት የፈተና ወቅት ሲመጣ ግን ሩጫው መስፈርት የሚያገኝበት አጋጣሚ መጣ እንደማለት ነው። ያኔ ምናልባትም ለራሱ አንደኛ እንደሆነ ያሰበው ሯጭ በእውነት ውራ እንደሆነ የሚረዳበት ቀን ሊመጣ ይችላል።

ለብቻ ማጥናት ተማሪው በመማር ሂደት ውስጥ በትኩረት ሊያደርገው የሚገባ እንቅስቃሴ ድርጊት ነው። ከሌሎች ጥረቶች በላቀ መልኩ እሱና መፅሃፍቱ የሚያደርጉት የአንድ ለአንድ ውይይት ለውጤቱ መማርና በትምህርትም ሆነ በስራ ዓለም ሊኖረው ለሚችለው ስኬት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ሆኖም ይህንን የግል ጥናት በአያሌ ሊደግፉ ከሚችሉ መላዎች አንዱ ጥናትን ከሌሎች ጋር ተቀራርቦ የማስኬዝ ነገር ነው። የህብረት ጥናት ለተማሪው ሊቸራቸው ከሚችለው ጠቀሜታዎች ጥቂቱን እንደ፦

*1. ተማሪው የግል ጥናቱን ለማስኬድ የሚጠው ተነሳሽነት* **(motivation)**፦ ይህን በህብረት ጥናት ውስጥ ሊያገኘው ይችላል። በተለይ የፈተና ጭምጭምታ ጎና ባልተሰማበት የትምህርት መጀመሪያና እኩሌታ ሰሞን በሙሉ

የሚያሳድርና ዋጋ ባለው መልኩ ጊዜን ለማዋል የሚረዳ ይሆናል። በየአንዳንዱ የጥናት ፕሮግራም ጅምር ላይ የሚፈጠር ግራ መጋባትንም ለማስወገድ ይረዳል። ከዚህ በተጨማሪ ውይይቱን የሚመራ አንድ ሰው በስምምነት መሰየም ጥናቱ ስርዓት የያዘ እንዲሆን ያስችላል።

*3. አጥኚ በዛ፣ ጥናት ጠነዛ:-* ለመሆኑ የህብረት ጥናት ግሩም ውጤትን እንዲያስገኝ ከተፈለገ የተሳታፊዎቹ ብዛት ምን ያክል መሆን አለበት? ይህ ጥያቄ በሁላችንም አእምሮ የሚመላለስ ሊሆን ይችላል። እንደ ህግ ቋሚ ቁጥርን መደንገግ ግትርነትና የተማሪውንና የትምህርት አይነቶችን ልዩነት ግምት ውስጥ የማያስገባ ይሆናል። ጥቅል መመሪያ መሰንዘር ግን ይቻላል- የጥናቱ ተሳታፊዎች ቁጥር መብዛት የለበትም!

ለቁጥሩ በተቻለ መጠን ማነስ ምክንያት የሚሆኑ ነጥቦች አሉ። አንዱ ብዛት ሲኖር ጥናትን የተደራጀ (organized) ለማድረግ የሚሳን መሆኑ ነው። ሃሳብን ሰብሰብ አድርጎ ውይይት የሚካሄድበት ነጥብ ላይ ትኩረትን ለመስጠት አዳጋች ይሆንና የሚፈጠሩት ትናንሽ የውይይት ንዑስ ግሩፖች ጠቅላላውን ሁኔታ የጨረባ ተዝካር ያስመስሉታል። መጯጯህና ጥቅል ሃሳብ ሳይይዙ መለያየቱ በአጥኚው ዘንድ ጊዜ የማባከንን ስሜት መፍጠሩ አይቀርም። ሌላው የፍጥነት ጉዳይ ነው። እያንዳንዱ የጥናቱ ተሳታፊ ያለው የመረዳት ፍጥነት እኩል ሊሆን አይችልም። ይህን ፍጥነት (pace) አስተካክሎ የመጓዝ ነገር ለተሳታፊው ሲበዛ አዳጋች ይሆናል፤ ፈጣኑ በሚዘገዩት የተነሳ ይሰላቻል፤ የሚዘገየው ደግሞ እንደተዋከበ ሊቆጥረው ይችላል፤ መጨረሻም ሁሉም የርካታ ስሜት ያጣና በህብረት የማጥናቱ ነገር አስፈላጊነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ያስገባዋል። ቁጥር አነስ ሲል ግን መናበብና ፍጥነት ይልቃሉ።

*4. በጥባጭ ካለ ጥሩ አይጠናም:-* የህብረት ጥናት የሚጠይቀው ሌላ የስርዓት ተገገርነት (discipline) ትኩረትን ከጥናት ላይ ነቅሎ ወደ ግላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች አለማዞርን ነው። በቅርብ የሚተዋወቁ ጓደኞች በሚገናኙበት አጋጣሚ የሚወያዩባቸውን ነጥቦች በጥናት ሰዓትም ዘው እንዲሉ በመፍቀድ የጥናት ፕሮግራሙን ሌላ የሳቅና የቧልት ጊዜ የማድረግ አዝማሚያ ሊኖራቸው ይችላል። ከደረቁ ትምህርት ነክ ጥናት ይልቅ ይህ አይነቶቹ ውይይቶች ይበልጥ ቀልብን የሚስቡ በመሆናቸው ይህን አዝማሚያ ፊዕሞ ማስቀረቱ አዳጋች ሊሆን ይችላል። ፕሮግራሙን በምንነድፍበት ወቅት እነህ ዓይነቶቹን የመዘናጊያ

መረጃዎችን ሳያካትት ሊቀር ስለሚችል የተሟላ ሊሆን አይችልም። ይህ «Recall pattern» ዘዴ ግን ትውስታን በማጎልበት ረገድ የተዋጣለት ሲሆን አንዳችም መረጃ ሳያጓድል በልዩ ንድፍ (Outline form) የሚያቀርብ ነው።

ይህን ዘዴ ለመጠቀም መመሪያዎች

1. የቶፒኩን ዋና ሃሳብ (Main idea) በባዶ ወረቀት መሃል ላይ ከሁለት ባልበለጡ ቃላት አስፍር፤ እንዲሁም የሚወክለውን አንድ ስዕል አስቀምጥ።
2. ከዚህ ከማዕከላዊው ዋና ሃሳብ የሚገነጠሉ ተባባሪ ሃሳቦችን በቅርንጫፍ መልክ ገንጥለህ አስፍር (Associated main idea)።
3. የአንድን መዘርዝር ሃሳብ የሚወክሉ ቁልፍ ቃላትን (Key word) ተጠቀም
4. የተረዳኸውን ዋና ሃሳብ ከሁን ቀደም ከሚታወቁ ተያያዥ ነገሮች (Previous related knolwedge) ጋር አያይዘው።
5. የፅሁፉ ንድፍ አቀራረብ ተነባቢ እንዲሆን በካፒታል ፊደል ተጠቀም።

የአሰራሩ ንድፍ ይህን ይመስላል



ለምሳሌ በአማርኛ «ሶስት» የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ «three» ነው፤ ሲነበብ ደግሞ «ትሪ» (iree) አይነት ዘይቤን ይይዛል:: «ትሪ» ዛፍ ሲሆን በዛፉ ላይ «3» ቁጥር በትልቁ ተፅፎ በህሊናህ ተመልከት:: ወደፊት «3» ምን እንደሚባል ለማስታወስ ስትፈልግ ዛፉ ትዝ ይልሃል (tree):: ዛፉን ስታስታውስ «three» ይመጣልሃል:: ሌላ ምሳሌ «ice» (በረዶ) የሚለው ቃል በስፓኒሽኛ «hielo» ሲሆን አነባበቡም «የሎው» ከሚለው ጋር ይቀራረባል:: በአዝነ ህሊናህ ውስጥ በስዕል «Yellow ice» በማለት ሳለው (ቢጫ በረዶ):: አሁን «ice» በስፓኒሽ ምን እንደሆነ ለማስታወስ ስትፈልግ «Yellow ice» ይሳልልሃል:: «Yellow» ደግሞ «Hielo» የሚለውን ቃል ትውስ እንዲልህ ያስገድድሃል:: ይህ አይነቱ የማያያዝ ስልት በህሊናህ ውስጥ እንደ ስዕል የምትመለከትበትን የትውስታ ዘዴ ይሰጥሃል:: ሌላ ምሳሌ፤ ጠመንጃ በእንግሊዝኛ «gun» ሲሆን ሲነበብ «ገን» ይሆናል:: «ገን» የሚለው ቃል «ጋን» ከሚለው የአማርኛ ስያሜ ጋር ይቀራረባል:: በህሊና ውስጥም በጋን ውስጥ ጠመንጃ ተቀምጦ ተመልከት:: አንዳንዴ እንዲህ ቀጥተኛ ምስስሎሽ ላታገኝ ትችላለህ:: ለምሳሌ «ብርቱካን» የሚለው ቃል በእንግሊዘኛ «Orange» ሲሆን ቃሉን አንዳች ምስል ፈጣሪ ቃል እንዲኖረው አድርገህ ስበረው፤ «o-range» የሚል ቃል ታገኛለህ:: «range»የሚለውን ውሰደው፤ «ሬንጅ» የሚል ቃል ይሰጥሃል:: በህሊናህ ውስጥም ብዙ ብርቱካኖች ሬንጅ በለበለ ስፋልት ላይ ተበትነው ተመልከት:: ለማስታወስ ስትፈልግ በአዝነ ህሊናህ ሬንጅ ላይ የተበተኑ ብርቱካኖች ይታዩሃል:: ሬንጅ ሲመጣልህ «ኦሬንጅ» ወይም «ኦራንጅ» ይታወስሃል ማለት ነው:: ሌላ ምሳሌ በአማርኛ «ምንጣፍ» የሚሰው ቃል በእንግሊዝኛ «Carpet» ይሆናል:: « Carpet» ሲገነጠል « Car-pet» ይሆናል:: በህሊናህ ውስጥ በመኪና (Car) አናት ላይ ምንጣፍ ተነጥፎ ተመልከት:: ይህ የማያያዝ ስልት በራሱ አስደሳች ሲሆን በህሊና ውስጥ ስዕላዊ ይዘት ስለሚቀርፅ ትውስታህን ያዳብራል::

ይህን የማያያዝ ስልት ለቃላት ክምችት መካበት በእጅጉ እንደሚረዳ የሚናገር አንድ የቋንቋ ጥናት ኤክስፐርት እንደሚለው ከሆነ አንድ ሰው አንድን ቋንቋ አውቂያለሁ ብሎ ለማለት የሚያስችሉትን ቃላት በዚህ ዘዴ በ10 ሰዓታት ውስጥ ማወቅ ይችልበታል ይላል:: አንድ ሰው ደግሞ አንድን ቋንቋ በሚገባ አውቄዋለሁ ለማለት ቢያንስ አንድ ሺህ ቃላቶችን ማወቅ አለበት:: እንግዲህ እንደባለሙያው እምነት አንድ ሰው በዚህ የማያያዝ ስልት አንድ ሺ ቃላትን በአስር ሰዓት ውስጥ ያውቅበታል ማለት ነው::

ቀደህ ከምትወስዳቸው መፅሐፉን እንዳለ ብትወስደው ይሻላል የሚል አባባል አለ:: ዋናው መታሰብ ያለበት አንተ መረጃዎቹን እንደምትፈልጋቸው ሁሉ ጓደኞችህ፣ ወደፊት የሚማሩ ተማሪዎች ወይም ልጆችህ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ አርቆ ማስተዋሉ ነው:: እንዲህ አይነት ባህሪያት ደግሞ በተለይ በኮሌጅ ደረጃ ለከባድ ቅጣት የሚያበቁ ናቸው:: እኔ እንኳን በኮሌጅ ቆይታየ ሶስት ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ የተባረሩ እንዳሉ ሲወራ ሰምቻለሁ:: አመት የተቀጡም ነበሩ:: በመሆኑም ብልህ ተማሪ ከእንዲህ አይነቱ አስነዋሪ ስህተት ራሱን ሊጠብቅ ግድ ነው::

**ስህተት 9:- ፈተና ወለድ ጭንቀት:-** እርግጥ ነው ፈተና ያስጨንቃል:: ይሁን እንጅ መጠኑ የበዛ መሆን የለበትም:: የፈተና ጭንቀት የሚጀምረው ፈተናው ቀናት ሲቀሩት ጀምሮ ነው:: ይህ መሆኑ ደግሞ ለፈተናው የሚደረገውን ዝግጅት የተምታታና ውጤት አልባ ያደርገዋል:: ይህን ለመግታት ቀደም ብሎ ያሉትን ጊዜያት ባግባቡ በመጠቀም ማጥናትና አጫጭር የማስታወሻ ኖቶችን ማዘጋጀት ነው:: ፈተናው ሲቃረብም እነዚህን መከለስ::

በፈተና ወቅት የሚታይ ጭንቀትም የፈተና አሰራር ላይ ከባድ ተፅዕኖን የሚፈጥር ነው:: ተማሪዎችን ለስህተት ከሚዳርጓቸው ምክንያቶች ውስጥ ጭንቀት የ30 በመቶ ድርሻ አለው:: ፈተና በራሱ ስሙ ቢያስጨንቅም፤ አንዳንዴ ጥያቄዎች ከበድ ብለው ሲታዩ ደግሞ የበለጠ መረበሽን ሊፈጥሩ ይችላሉ:: እወድቅ ይሆን ወይም «A» ግሬድ አገኝ ይሆን የሚሉም ስሜቶች እንዲሁ የሚረበሹ መንስኤዎች ናቸው::

ዋናው መፍትሔ ከፈተናው በፊት በበቂ ሁኔታ መዘጋጀት፣ በራስ መተማመንና አስፈላጊውን ጥናት እስካከናወኑ ድረስ ውጤቱ የፈለገው ይሁን የሚል መንፈስን ማጐልበት ነው:: በሚገባ ያጠና ተማሪ ውጤቱ ለመርቂ እንደሚሆን መዘንጋት የለበትም:: ይልቁንስ በመጨነቁ የለፋበትን ጥናት ገደል ሊከተው ይችላል:: በመጨነቅ አንዳችም ትርፍ አይገኝም:: መጨነቅ የሚጠቅመው ቀድሞ ስለሚደረገው የጥናት ሂደት ላይ ብቻ ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች በፈተና ወቅት ስለሚመጣው ውጤት ሳይጨነቁ በራስ መተማመን መንፈስ ፈተናን መስራት ነው::

ተማሪዎች በፈተና ወቅት ሲጨነቁ አጭር ፀሎት ማድረግና ሶስት ጊዜ ጥልቅ ወደ ውስጥ መተንፈስ ህሊናቸው ዘና እንዲል ይረዳቸዋል:: እንዲሁም

ጭንቀትና መረበሽ የሚጠነክርበት ተማሪ ከፈተና አንድ ሰዓት ቀደም ብሎ 40 ሚ.ግ ፕሮፕራኖሎል ኪኒን ቢወስድም ጥሩ ነው።

**ስህተት 10:- መዘናጋት**:- መዘናጋት ብዙ ጊዜ አለኝ በማለት ከሰር ከሰሩ የማጥናት ልምድ ካለመኖር የሚፈጠር ነው። ስርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ በመሆን ፈተና ሲቃረብ መራወጥ የሰነፍ ተማሪ ምልክት ነው። ስለፈተና መታሰብ ያለበት ገና ትምህርት ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ ነው።

መዘናጋትን ከሚፈጥሩ ነገሮች ውስጥ መዝናናት ማብዛት፣ ማህበራዊ ህይወት ማብዛት፣ እንቅልፍ መውደድ፣ ብዙ ጊዜያቶች አሉኝ በሚል እሳቤ ራስን ማታለል፣ ሳብጀክቱን አቅልሎ መመልከት ይገኙበታል። እንዲሁም ጥናትን በጊዜ ሰሌዳ በማስመርኮዝ በእቅድ ያለማጥናት ልማድም ለዚህ ያጋልጣል። አለበለዚያ ግን ፈተና ሲቃረብ ከላይ ከታች እያሉ ቢራወጡት እርባና የለውም።

**ስህተት 11:- ሽምደዳ**:- የመማር ማስተማር ሂደትን ስኬታማ ከሚያደርጉት አብይ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ሽምደዳ መሆኑ አይካድም። ይሁንና ሽምደዳ ከመልካም አረዳድ ጋር ካልታጀበ ግን ከንቱ ነው።

«Adequate learning= memorization "+" understanding» የምትሰኘዋ ቀመር ለዚህ አብነት ነች። አንድ ተማሪ ስለሸመደደ ብቻ ትምህርቱን አውቂዋለሁ ሊል አይችልም። አብዛኛውን ጊዜ ሰፊ ድርሻ ያለው ፅንሰ ሃሳቡን በጥልቀት መረዳት ሲሆን እንደ ታሪክ፣ ሲቪክስና ጆግራፊ አይነት ትምህርቶች ደግሞ ሽምደዳ አመዛኙን ቦታ ሊይዝ ይችላል። በጥናት ረገድ ፅንሰ ሃሳብን በደንብ ተረድቶ መረሳት የሌለባቸውን አንኳር ጉዳዮችን (ስሞችን፣ ዝርዝሮችን፣ ቁጥሮችን፣ ቀመሮችን) ደግሞ መሸምደድ ይገባል። በመሆኑም ሽምደዳ ላይ ብቻ ያተኮረ ጥናትን የሚከውን ተማሪ ከባድ ስህተት እየፈፀመ እንደሚገኝ ማወቅ ይገባዋል።



# ስኬታማ የትውስታ ጥበቦች

የሚፈለገውን ሁሉ በአንዴ ንባብ ብቻ እስከወዲያኛው ለማስታወስ

ተያያዥነትን የመፍጠር ዘዴ ሲሆን ጠቀሜታው ለማስታወስ ብቻ ሳይሆን መረጃውን ስንፈልገውም እንደልብ ማውጣትና መጠቀም እንድንችል ያግዛል::

**8. *ከሰፊው ወደ ጠባቡ ሂድ (Funnel approach)*:-** ይህ ስልት እንደሚመክረው ከሆነ አንድን ቶፒክ ለማስታወስ በሚል መልኩ ስናጠና መጀመሪያ በውስጡ ስላሉት አንኳር ጉዳዮች ከመጨነቅ በፊት የቶፒኩን አጠቃላይ ፅንስ ሃሳብ መረዳትን ማስቀደም ይመክራል:: መሰረታዊ ጭብጡንና የቶፒኩን ዋና አከርካሪ ከመሰረትን በኋላ ጠለቅ ወዳሉ አስረጅዎች (details) ቀጥለን በመግባት የቶፒኩ አከርካሬ ነፍስ እንዲዘራና የተሟላ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል:: ይህን በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል:: አንድን ቶፒክ ስናነብ መጀመሪያ ገረፍ ገረፍ ካደረግን በኋላና አጠቃላይ ግንዛቤ ከጨበጥን በኋላ ነው ወደ ዝርዝር ጉዳዩ የምናመራው:: የመፅሐፎችን አፃፃፍ ተመልከታችሁም ከሆነ ከአጠቃላይ አስረጅነት ወደ ዝርዝር ጉዳይ ነው የሚያመሩት:: በመሆኑም በቅድሚያ የቶፒኩን መሰረታዊ አንኳር ጉዳይ ካወጣንና ከቀረፅን በኋላ ዝርዝር ጉዳዮች እያመጡ በጎደለ የመሙላት ስልት የተውስታና የግንዛቤ ብቃትን ያዳብራል::

**9. *ትርጉምን ከገሃዱ ዓለም ጋር አስተሳሰር (Meaning association)*:-** ትምህርት እየተማርን ባለንበት ወቅት የሚሰጠንን አዲስ መረጃ ካሁን ቀደም ካለን እቲያይ ጋር የማስተሳሰር ባህሪ አለን:: ለምሳሌ የተማርነውን መረጃ ከምንኖርበት አካባቢ ጋር፣ ከህሊናችን ቀደምት አመለካከት ጋር እንዲሁም ከምናባዊ ሃሳቦቻችን ጋር እያነፃፀርን፣ እያጣመርንና እያስተሳሰርን እንሄዳለን:: ለምሳሌ ቁልፍ ረስተን ከሆነ ቁልፉን ጠረንጴዛ ላይ ወይም ቦርሳ ውስጥ እንዴት እንዳስቀመጥን በማውጠንጠን የት እንደረሳነው ሁታውን እንደርስበታለን:: ይህ ነው እንግዲህ ማስተሳሰር:: የቁልፉን አቀማመጥ ለማስታወስ አካባቢያዊ ትውስታን ተመርኩዘን ማለት ነው:: እና አንድ ተማሪም ሲያጠና በዚህ መልክ ለማስታወስ ሆን ብሎ መረጃውን ማስተሳሰር ይኖርበታል። ለማስታወስ ሲፈልግም መረጃውን ከምን ጋር እንዳስተሳሰረው በማጤን ሊያስታውሰው ይችላል:: ማለትም ህሊናዊ ቅኝትን ተጠቀም ማለት ነው::

በተጠናው አዲስ ፅንስ ሃሳብ ዙሪያ የበለጠ ጥልቅ የሆነ ትውስታን ለመፍጠር መረጃውን ትርጉም ባለው መልኩ ከራስ ጋር ማያያዝ ነው:: ለምሳሉ እንደ አንተ አመለካከት መረጃው ምን ትርጉምና ምን ጠቀሜታ እንደሚሰጥህ፣

አንድ ተማሪ ነበረች:: የ«Quadratic equation formula:-$y = ax^2 + bx + C$» በዜማ መልክ ዘፈን አውጥታ መሸምደድ ችላ ነበር (10ኛ ክፍል እያለን)::

በተሰይ ዘዴው ዜማ መፍጠር ለሚችሉ ተማሪዎች ከማስታወሻነቱ በተጨማሪም አዝናኝነት አለው:: ዘፈን አይደል? እንዲሁም የግጥም አይነት ዘይቤ እንዲኖረውም ማድረግ ይቻላል:: ለምሳሌ 30 ቀናት ያላቸውን የነጮች ወራት ለማስታወስ፤

«30 days have September,
April June and November.»

ዜማ መፍጠር ለማይችሉ ደግሞ የሚያውቁትን የዘፈን ዜማ መገልገል ይችላሉ (በኮፒ ራይት ህግ ላለመያዝ ግን እየተጠነቀቅን)::

## 4. አካባቢያዊ ትውስታን መጠቀም (method of loci):-

ይህ የትውስታ ቴክኒክ ከህዝብ ፊት ለሚደረግ ንግግር ጥንታውያን አፈ ቀላጤዎች ይጠቀሙበት የነበረ ነው:: ዘዴው ተከታታይነት ያላቸውን ዝርዝር (List) መረጃዎች ማቀዳጀት፣ ምስላዊ የትውስታ ዘዴዎች የሚጠቀም፣ እንዲሁም ማስተሳሰርን የሚጠቀም ነው::

ይህን ዘዴ ከመጠቀምህ በፊት አንድ የታወቀና በተደጋጋሚ የምትጠቀምበትን ጉዳና ምረጥ:: ከዚያም በጉዳናው መጀመሪያና መጨረሻ መሃከል ያሉ ወሳኝና ቋሚ ምልክቶችን ለይተህ አስቀምጥ:: አላማው ለማስታወስ የምትፈልጋቸውን ዝርዝር መረጃዎች በእነዚህ በተመረጡ ዋና ዋና የጎዳናው ምልክቶች ጋር ትርጉማዊ ተያያዥነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው:: ይህን ትስስር አንዴ ከፈጠርክ በኋላ ዝርዝር መረጃዎቹን ለማስታወስ ስትፈልግ በሀሊናህ ራስህን በጎዳናው ላይ እየሄድክ ማየት ነው:: እንዲህም ስታደርግ ዋና ዋና የጉዳናው ምልክቶችን ታገኛለህ:: ምልክቶቹንም ስታገኝ ከእነሱ ጋር የተሳሰሩትን መረጃዎች በቀላሉ ታስታውሳቸዋለህ ማለት ነው::

ለምሳሌ ብዙ ጊዜ የምትጠቀምበት ጎዳና ከቤት ወደ ት/ቤት የምትጓዝበት ሊሆን ይችላል:: በዚህ ጎዳና ላይ ከቤትህ ቀጥሎ የአውቶቡስ ፌርማታ ይኖራል እንበል:: ከዚያም ቀጥሎ አንድ የታወቀ ወይም ትልቅ ሆቴል ታገኛለህ እንበል:: በመቀጠል ትልቅ የዋርካ ዛፍ ይገኛል፣ ከዚያም ቀጥሎ ሃውልት ... እያልክ በመጨረሻ ት/ቤትህ ትደርሳለህ::

አሁን የጎዳናዎቹን ወሳኝ ምልክቶች እንጥቀስ:- መኖሪያ ቤት፣ የአውቶቡስ ፌርማታ፣ ሆቴል፣ ዋርካ ዛፍ፣ ሐውልትና ት/ቤት ናቸው:: ማስታወስ የምትፈልጋቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው እንበል:- ብርቱካን፣ ጋሪ፣ ሚሰባር፣ ልብስ፣ ኳስና ጫማ:: ቀጣዩ ስራ ዝርዝሮቹን መረጃዎች ከጎዳናው ምልክቶች ጋር አንዳች ትርጉማዊ ትስስሮሽ

5. የልዑንዳ ቤቶች ሥጋ መስቀያ (ሜንጠ)
6. የቴኒስ ኳስ ራኬት (ራኬት)
7. የገደል አፋፍ (ገደል)
8. ወገበ ቀጭን ሴት (ሴት)
9. ጅራታም ባሉን ወይም ፊኛ (ባሉን)
10. ባለ አንድ ቀዳዳ (ቀዳዳ)

በዚህም መሰረት:- 1. (ሻማ)፣ 2. (ሰንን)፣ 3. (መነፅር)፣ 4. (ቀስት)፣ 5. (ሜንጠ)፣ 6. (ራኬት)፣ 7. (ገደል)፣ 8. (ሴት)፣ 9. (ባሉን)፣ 10 (ቀዳዳ) ይሆናሉ::

ቀጣዩ ሥራ መታወስ ያለባቸውን ዝርዝር መረጃዎች ከቁጥሮቹ ትርጓሚ ስያሜዎች ጋር ምስላዊ ትስስሮሽን መፍጠር ነው::

## 8. የፊደላት ትውስታ ዘዴን መጠቀም

**(alphabet system):-** ይህ ደግሞ ሌላኛው አይነት ስልት ሲሆን እዚህ ጋር ግን የማንተራሻ ስሞችን የምናገኘው የአልፋ ቤቱን አነባበብ ወደ ቃል በመለወጥ ነው:: የሚመሰረተው ቃል ግን ምናባዊ (abstract) ሳይሆን ተጨባጭ መሆን አለበት:: ለምሳሌ:-

A- Aeroplane
B - Bee
C- Sea
D- Diesel engine
E- Eel
F- Effluent
G-Jeans
H- H-bomb
I - Eye
J- Jet
K- Cake
L- Elephant
M- Empty
N- Entrance
O- Ox
P- Pea
Q- Queen
R-Are
S- Eskimo
T- Tea
U-Uterus
V- Vehicle
W- WWW. Com (Internet)
X- X-ray
Y- wire
Z- Zebra

ይህ ስልት ቢ... እስከ 26 ዝርዝር መረጃዎችን እንድናስታውስበት ይጠቅማ... ...መጠቀማችን ... ...ን ፊደላቱንና የሚወክሏቸውን ቃላት በሚገባ

መገንዘብ ያስፈልጋል:: በመቀጠልም ከዝርዝሩ መረጃ ጋር ምስላዊ ትስስርን መፍጠር ነው:: ማስታወስ ሲፈለግም መረጃውን ከአእምሮ ለማውጣት የአልፋ ቤቱን ቅደም ተከተል እየጠሩ መገንዘ ነው::

## 9. የአልፋቤትና ቅርፃቸው አጠቃቀም

**(Alphabet/shape system):-** ይህ ልክ እንደ ቁጥር ቅርፆች ዓይነት ነው::

ለምሳሌ:-

A - ጎጆ

B - መነፀር

C - ማጭድ

D - የአምፒሲሊን ግማሽ (አምፒሲሊን)

E - ሹካ

F - ባንዲራ.. እያለ ይቀጥላል::

**10. የማጣመር ቴክኒክ (chunking):-** ይህ ስልት በተለይ ጠቀሜታው ረጅም ቁጥሮችን በቀላሉ ለማስታወስ ነው:: ለምሳሌ ተፈጥሯዊውን የቴሌፎን ቁጥር የማስታወስ ባህሪያችን ሁለት ቁጥሮችን ለየብቻቸው በመጥራት ነው::

ምሳሌ:- ቴሌፎን ቁጥሩ «275678» ቢሆን እኛ ግን የምናስታውሰው እያንዳንዷን ቁጥር በመጥራት ሳይሆን «27-56-78» በማለት ነው:: የዚህም በማጣመር ቁጥሮችን የማስታወስ ዘዴ እንዲሁ ነው:: በተጨማሪም የቁጥሮችን ልዩ የአደራደር ባህሪ ማጤንም ሌላው ስልት ነው::

ለምሳሌ የሚታወሰው ቁጥር «64831996» ከሆነ ለሁለት በመክፈል «6483-1996» ልንለው እንችላለን:: «1996»ን የአመተ ምህረት መጠሪያ አድርገን ካሰብነው ቁጥሩ በቀላሉ ይታወሰናል ማለት ነው:: «719819919» ቁጥርን ለማስታወስ የአደራደሩን ዜደት በመቀየር ለትውስታ ማመቻቸት እንችላለን:: ለምሳሌ «7/19,8/19,9/19»(7፡8፡9 ተከታታይ ሲሆኑ «19» ቁጥር ግን ቋሚ ነው:: ስለዚህ «7,8,9»)ን ከያዝን በእነዚህ መሃል«19» ቁጥርን መጨመር ይሆናል::

«2100200» ቢሆን ለማስታወስ «21-00,2-00» በማድረግ ልንጠራው እንችላለን::



# ስኬታማ የፈተና አሰራር ምስጢሮች

ብዙ ሳይደክሙ ለከፍተኛ ውጤት
የሚያበቁ ጥበቦች

→ ጧት ደግሞ ከአንድ ሠዓት በፊት ቀደም ብለህ ተነስ!

12. የፈተናው ቀን፡-

ይህ ቀን በጉጉት ሲጠበቅ የነበረ ሲሆን በሦስት የተለያዩ የጊዜ ሠሌዳዎች ለያይተን እንመለከተዋለን።

## 2.1 የጣት ፈተና አሠራር ምስጢር

ከፈተና ጊዜያቶች ሁሉ የጧት ፈተና እጅግ ተመራጩ ነው። ምክንያቱም ከጥሩ እንቅልፍና የህሊና እረፍት በኋላ ያለ በመሆኑና ቅር የሚሰኝን ቶፒክ ሳጥና የሚል ስሜት ቢኖር እንኳን ራስን ለመወጠሪያ ሰዓቱም የለምና ነው። ከፈተናው መጀመሪያ በፊት በአንድ ሰዓት ልዩነት ከመኝታህ ተነሳ። ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ብለህ ማልደህ መነሳት ራስህን ለጭንቀት መጋበዝ ሲሆን ከዚህ ያነሰ ሰዓት ካለህ ደግሞ «ረፈደብኝ» በሚል መንፈስ ራስህን ላለመረጋጋት ትጋብዛለህ።

በዚህ ሠዓት ውስጥ የሚኖሩህ ዋና ዋና ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የክለሳ ኖቶችህን አንዴ ገርፍ ገረፍ አድርግበት፤ ይህ ጠቀሜታው ለማስታወስ ወይም ለመከለስ ብቻ ሳይሆን ጥልቁ የአንጎል ክፍል (Subconcious) ለፈተናው ዝግጁ እንዲሆን ደወል ለማሰማት ነው።
- ቀለል ያለና ጥሩ ቁርስ መመገብ ይኖርብሃል። ይህ የሚጠቅምህ አንጎል ለሚገጥመው ፈተና ጥሩ ኃይል እንዲኖረው ያግዝሃልና ነው (አንጎል ከሰውነታችን ውስጥ ከፍተኛ የግሉኮስ ተጠቃሚ ነው፤ ስለሆነም ጥሩ እንዲሠራልህ ጥሩ አድርገህ አብላው)።
- የቻልከውን ሁሉ አድርገሃል፤ ስለዚህ በዚህች ሰዓት መጨነቅ ትርጉም ስለሌለው ራስህን አዝናናው እንጂ በፍርሃት ራስህን አታስጨንቀው።

<u>በአጭሩ፡-</u>

- አንድ ሠዓት ቀደም ብለህ ተነሳ
- የክለሳ ኖቶችህን አንዴ ግረፋቸው
- ጥሩ ቁርስ ብላ

## 2.2 የከሠዓት ፈተና አሠራር ምስጢራት

የፈተናው ቀን እንደዛሬ ሆኖ ነገር ግን ፈተናው የሚወሰደው ከሰዓት ከሆነ ብቻ ወይም ጧት ነፃ የሆነ ክፍለ ጊዜ ካለ የራሱ የአሠራር ምስጢር አለው።

... የአጻጻፍ ስልት ... ፈተናውን መስጠት ነው። አሁን እንዴ
... ተማሪ ማድረግ ያለበ...
... ከማስጀመሩ በፊት ... እርግጠኛ እንዲሁም በግልፅ ... ሰዓት ይይዛል፤ ቀጥሎም ... ለማስቀመጥ በመቀጠል ወደ ተቀሪ ... በተሰጠው ሰዓት ከማለቁ በፊት ... ተማሪዎች እንደዚሁ ነው። ... ፈተና ላይ ያለ ተማሪ ... ፈተና እየተፈተኑ ያሉ ተማሪ ... እንደ አንድ እቅድ (Organized Plan) ያስፈልገዋል፤ ይህም ... የተቀናጀ እቅድ ... በሚገባ ለመወጣትም ነው። ... ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፤ ... የፈተናውን ... ለማንበብ ጊዜ ... አዕምሮ የጥያቄውን ሁኔታ ... መልስ የሚሻ (Short Answer) ... ያስፈልጋል። ጥያቄው ... ጥያቄውን በሚገባ ሳይረዱ ወይም ... የሚፈልግ ... አይደለም። በአጠቃላይ ሁሉንም ... ለማግኘት ... ተገቢ ... በስነ መንፈስ ማስኬድ ለፈተና ውጤታማ ውጤቶች ጊዜ በመስጠት ... ችሎታቸውን ማስወገድ የለባቸውም፤ ያደርጋል። ስለዚህ ተማሪዎች በፈተና ጊዜ ... የሚቀርቡ ስለሆነ ... ጊዜና ... ምንጊዜም ... ነገር አይደለም።

# የኢሲይ ፈተናዎች አሰራር ምስጢር

በውጭ ሀገር ትምህርቶች (በተለይ እንግሊዝኛ) ላይ ረጃጅም ፅሁፎችን የሚያዘጋጁ ተማሪዎች የሚመጡ ጥያቄዎች እንዲመልሱ መጠየቅ በአብዛኛው ፈተና የሚደረግበት ነው። በእንግሊዝኛ ወይም በሌሎች የባዕድ ቋንቋዎች ብቻም ሳይሆን በአማርኛ ቋንቋችንም ቢሆንም ስለ ጉዳዮችና ግጥሞች ውስጥ ጥያቄ በማውጣት ... ነገር አዲስ አይደለም። እናም ተማሪዎች እንዲህን ሁኔታዎች በመገንዘብ ... ም ሆነ ረጅም ስለ ጉዳዮችን የማገናዘብ ባህላቸውን ማዳበር ቢችሉ በእንደዚህ ... ሁኔታ ሊያገኙቸው የሚችሉ ፈተናዎችን የመመለስ ብቃታቸውን ያሳድጋሉ።

[illegible]

ፈተናው ከባድ ቢሆን ለማንኛውም አትጨነቅ። ከባድ ፈተናዎች የሚከብዱት ላንተ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ነው። ይህም መሆኑ ደግሞ የተማሪዎችን አማካይ ውጤት ዝቅ ሊያደርገው እንደሚችልም አትጠራጠር። አስተማሪዎች እንዲህ ዓይነት ኢ-ጠጣኝ ሲመለከቱም የግሬድ (ከሌሎች ጋር) የማለፊያ ነጥቡን ዝቅ ማድረጋቸው አይቀሬ ይሆናል።

ከፈተና አዳራሽ እንደወጣህም ጓደኞችህ ፈተናውን እንዴት እንደሰሩት ለመጠየቅ ብትሞክር እንኳን የተደበላለቀ ምላሽን እንደምታገኝ አትጠራጠር። ዋናው ነገር አንተ የቻልከውንና በጥናት የደከምከውን ያህል ፈተናውንም በሚቻለው መልኩ ሠርተኸው እስከወጣህ ድረስ ሌሎች ስለፈተናው የሚናገሩትም ስሜት ተመሳሳይ ነው። በአንዳንድ አስመሳዮችም አትደናገር።

ባህሪያቸው ሆኖ አንዳንዶቹ ፈተናው በጣም እንደቀለላቸው የሚያናፍሱ አሉ። አትጠራጠር ውጤቱ ሲለጠፍ ግን ስማቸው ከታች ተደርድሮ ታገኘዋለህ። እነዚህ እንግዲህ በቅፅል ስማቸው «የታች መንደር ሰቃዮች» የሚባሉት ናቸው። እናም ከፈተና ሲወጡ «አቦ የባሬው ፈተና እንዴት ይመቻል!» ሲሉ ልትሰማቸው ትችላለህ። የሰሩትን ስለሚያውቁት ራሳቸውን ለማፅናናት የሚሏት ናትና (Defense Mechanism) በልብህ ሳቅባቸው።

ይህንን የድህረ ፈተና ጊዜ (Post Exam) ራስህን ለማዝናናት ተጠቀምበት እንጂ ህሊናህን አትረብሽበት። ይህቹ ጊዜ ፈተና የጨረስክባትና፣ ለሌላ ወሳኝ ሥራ ከመዘጋጀትህ በፊት ያለች ናትና ተዝናናባት። ፈተናው ቢከብድህም፣ መሥራት ያለብህን ነገር ባትሠራም እንኳን ውስጣዊ ረብሻህን ለመርሳት ሞክር።

# የፈተናዎች ሁሉ 32 ህጎች

ምንም እንኳን ለእያንዳንዱ የፈተና አይነት የአሠራር ሁኔታ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሰፊው የተዳሰሰ ቢሆንም ተማሪዎች ወደፈተና ከመግባታቸው በፊት በጥንቃቄ እንዲከልሷቸው ወሳኝና የማይረሱ ነጥቦችን በአጭሩ ማቅረብ ተመራጭ ሆኖ በመገኘቱ በሚከተለው መልክ ተቀርፀዋል። እነዚህንም መሰረታዊ ህጎች ግን ጊዜም በፈተና በፊት እንደ በማንበብ ተጠቀምባቸው። የጥናትህ አንድ አካል ናቸው እነሆ፦

1. በመጨረሻዋ የፈተና ደቂቃ ከለሳ ይቁም
2. ወደፈተና ከመግባትህ በፊት ራስህን አዝናናው
3. የፈተናውን መጀመሪያ ሠዓትና ቦታ ቀድመህ እወቅ
4. ከፈተናው መጀመሪያ ሰዓት በፊት ድረስ
5. በሌሎች ተማሪዎች ልብ መሉነት አትያዝ
6. ወደፈተና ከመግባትህ በፊት አንዴ የሬቪዥን ጥቆችህን ግለጻቸው
7. በዚህ ሠዓት ከሌሎች ተማሪዎች ጋር አትወያይ
8. ወደ ውስጥ በጥልቀት እየተነፈስክ ራስህን አረጋጋ፤ ጥሩ ጥሩ ነገርንም አስብ
9. የእጅ ሠዓት ይኑርህ፤ በትክክል መቁጠሩንም አረጋግጥ
10. ትርፍ እስክርቢቶና እርሳሶች መያዝህን አስታውስ
11. የፈተና ወረቀቶቹን ብዛት ትክክል መሆናቸውን አረጋግጥ
12. የጥያቄዎቹን ትዕዛዝ በጥሞና አንብብ
13. የጥያቄዎቹ አጠቃላይ ቁጥር ትክክል መሆኑን አረጋግጥ
14. ከፈተና ወረቀቱ ጀርባ ቀሪ ጥያቄዎች አለመኖራቸውን አረጋግጥ
15. ለፈተናው የተፈቀደውን ጊዜ እወቅ
16. ለያጥያቄዎቹ ሠዓት መድብ፤ ትርፍ ጊዜ ለክለሳም አስተርፍ
17. መመለስ ከመጀመርህ በፊት ሁሉንም ጥያቄዎች ቀድመህ አንብብ
18. የጥያቄዎቹን አይነትና የማርክ አሰጣጥ ደንባቸውን አጢን
19. ቀላል ጥያቄዎችን በቅድሚያ ሥራ
20. መልሶችህ ተነባቢና ግልፅ ይሁኑ
21. ከተረበሽክና ከተጨነክ መስራትህን አቁመውና ራስህን ዘና ለማድረግ ጣር

አስተያየቶች የሁሉንም አዲስ ትምህርት ፈላጊ ሁኔታ በአንድነት ሊወክሉ አይችሉም:: ሆኖም አንባብያን እናንተን በተለይ ሊመለከት በሚችል መልኩ የቀረቡት ሃሳቦች እንድትወስዷቸው እጠቁማለሁ::

*1. አቅምዎን ያገናዝቡ:-* ትምህርት ዋጋ የሚያስከ ፍል ነገር ነው:: ቢያንስ ለጥቂት አመታት ቀጣይነት የሚኖረው የኮሌጅ ትምህርት ደግሞ የሚያስከፍለው ዋጋ ላቅ ያለ ነው:: ኮሌጅ ለመምረጥ በምንዘጋጅበት ሰዓት በቅድሚያ ራሳችንን ልንጠይቅ የሚገባው ጥያቄም «ለመርጠው ያሰብኩት የትምህርት ዘርፍ የሚጠይቃቸውን ነገሮች ለአመታት ሊዘልቅ በሚችል መልኩ የሚያሟላ አቅም አለኝ ወይ?» የሚለውን ነው::

አቅም(potential) የሚለው ቃል እዚህ ላይ የሚወክለው በርካታ ነገሮችን ነው:: ኮሌጆቹ የሚጠይቁት የመመ ዝገቢያ መስፈርት ውጤት የመጀመሪያው ነው:: ይህን የሚያሟላ ውጤት ሲኖር ወደሌሎቹ ነጥቦች እናልፋለን:: ብቃት የሚቀጥለው ነጥብ ነው:: በትምህርት ላይ ያለንን ብቃት ለራሳችን ታማኝ ሆነን ማገናዘብ በእጅጉ አስፈላጊ ነው:: ከአቅም በላይ የሆነን የትምህርት ዓይነት ውጤት ስላለን ብቻ መምረጥ ውሎ አድሮ ለስኬት ማጣትና ለማፈግ ፈግ ምክንያት ሊሆን ይችላል::

ጊዜ ሌላው የአቅም መስፈርት ነው:: የከፍተኛ ተቋም ትምህርት ከወትሮው የተለየ የጥናትና የስራ ሰዓትን ይጠይቃል:: ተመዝጋቢውም ያለውን የጊዜ መጠን የሚያሰላው በትምህርት ላይ የሚያሳልፋቸው ጊዜዎች ላይ ብቻ በመመስረት መሆን የለበትም:: ይህ በተለይ ቋሚ ስራ ያላቸውንና በትርፍ ሰዓት ለመማር የወሰኑትን ይመለከታል:: «ለመሆኑ ይህን የትምህርት ዘርፍ ብመርጥ የሚጠይቀውን የጥናትና ልምምድ ጊዜ የያዝኩትን ስራ ሳልበድል ማሟላት እችላለሁ?» ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ይኖርብናል::

የገንዘብ አቅምም ሌላው ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ነው:: ይህ በተለይ በግል ትምህርት ተቋማት ለመመዝገብ ዕቅድ የያዙትን ይመለከታል:: የኮሌጅ ትምህርት ለረጅም ጊዜ የሚቆይ በመሆኑ ያለን የገንዘብ አቅም ቀጣይነት ያለውና በቂ መሆኑን ማገናዘብ አግባብ ነው:: ለትምህርት ከሚከፈለው ገንዘብ ባሻገር ቁሳቁስ ለማሟላት፣ ለትራንስፖርት... የሚወጡ ሽርፍራፊ ወጪዎችንም ማስታወስ ያስፈልጋል:: ለምርጫ ያጨናቸው ኮሌጆች መሃል ያለውን የወጪ ልዩነት ማወዳደር፣ ወጪውን ለሚሸፍንልን አካል (ራስ፣ቤተሰብ....) ደግሞ መቅርቀር ይኖርብናል::

3. *ፍላጐት ወይስ ኪስ?* የምንመርጠውን የትምህርት ዘርፍ ስናስብ ካለን መረጃና የአቅም ሁኔታ ባሻገር የምናገኘው ዝንባሌያችንን ነው:: ዝንባሌ (inclination) በየትኛው ዘርፍ ትምህርታችንን ብናስኬድና ኑሯችንን ብንመሰርት መልካም እንደሚሆን ውስጣችን የሚሰጠን ጥቆማ ነው:: ይህን ነጥብ ቸል ማለት አደጋ አለው:: ከዝንባሌ ይልቅ ግፊትንና የተሻለ የኑሮ እርከን ትንቢትን ተከትሎ መጓዝ ፈፅሞ ለራስ ሊስማማ በማይችል ዘርፍ ውስጥ ገብቶ ያለዕርካታ መዳከርን ሊያስከትል ይችላል::

እዚህ ጋር በባለቤቱ ዘንድ ያለው ፍላጐትና ዝንባሌ በትክክለኛው አቅጣጫ መሄዱን ልብ ማለትም ይገባል:: አሁንም ለዚህ አከርካሪ የሚሆነው የበቂ መረጃ መኖር ነው:: ስለአንድ የትምህርትና እሱን ተከትሎ የሚመጣ የስራ ዘርፍ በቂ እውቀት ሲኖር ብቻ በእርግጠኝነት ዝንባሌዬ ነው ወይም አይደለም ብሎ መናገር ይቻላል::

ይህን በተመለከተ አስተማማኝ እውቀትና እርግጠኝነት ሲኖረን «ከዝንባሌዬና እሱ ከሚያሳጣኝ የኑሮ ምቾት የትኛው ይሻለኛል?» ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን:: ለዚህ ጥያቄ የሚኖረን ምላሽ ዕውነታውን አርቆ የተመለከተ መሆን አለበት:: በምርቃት ማግስት የሚገኝ የስራ ዕድልን ብቻ ሳይሆን ከኮርሱ በስቲያ የሚኖር የህይወት ማሻሻያ ዕድልና እድገትንም ማሰላሰል ያስፈልጋል:: ነገን ብቻ ሳይሆን ከነገ ወዲያንም ጭምር እንደማሰብ ማለት ነው::

እንግዲህ በመጨረሻ ልናደርገው የሚገባው ነገር የመረጥነውን የትምህርት ዘርፍና ኮሌጅ ዝንባሌን፣ አቅምንና የወደፊት ኑሮን አገናዝበን መለካት ነው:: ይህን ማድረግ ስንችል በቅጡ አጠናን ያደረግነው ስለሆነ በምርጫችን መፀፀት እናቆማለን::

«አስቦ የሚራመድ ሩቅ መንገድ ይጓዛል»

# የመመረቂና ጥናታዊ ፅሁፎች የአዘገጃጀት ስልቶች

በጥናታዊ ፅሁፍም ሆነ በሌላ ሪፖርት መፃፍ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ዙሪያ የሚቀርብ ሪፖርት የሚከተሉት መንገዶች መከተል እንደሚኖርበት ይታመናል:: ይህ ካልሆነ ግን አጠቃላይ የሃሳብ መዘበራረቅንና በተገቢው መንገድ እንዲሁም ቅደም ተከተሉን ያልጠበቀና የተዘበራረቀ ሃሳብን ከማስከተል አልፎ ጊዜንም ያለ አግባብ ሊያባክን ይቻላል::

*ሠመሪያዎች* **(Guide lines)**

ዶ/ር አበበ [illegible]

[illegible]

ዋና አዘጋጅ



የሒሳብ ትምህርቶችን በቀላሉ እንዴት ማስተር ማድረግ ይቻላል?

በትንሽ ጥናት፣ ብዙ ፈተና በብቃት የመወጣት ምስጢሩ ምንድን ነው?



እንደን መጽሐፍ ከዳር ለስከዳር ከግንባቢ ጋር መሸምደደ እንዴት ይቻላል?

የትኛውንም ቋንቋ በአጭር ቀናት ውስጥ እንዴት ማወቅ ይቻላል?

[illegible]

ከ20 በላይ የሚደርሱ ዝርዝር መረጃዎችን፣ ረጃጅም ቁጥሮችን እንዲሁም ሁሉ ፃታታዎችን እስከወዲያኛው ለቅም ለማስታወስ ሳይንሳዊ ዘዴው ምንድን ነው?

ዋጋው ብር 17.00